# የኛ ሰው - ጣጤ

ጌታቸው አባሙዳ - ከ ዩጋንዳ

የኛ ሰፈር ሰው ሲጠጣ
ያሰኘዋል ማረጥረጥ፣ ዳንኪራ መርገጥ
መዘላበድ ፣ መቀላመድ - አንደበቱን መለጠጥ

ጥምቢራው ሲወጣ - ሲለይለት
ይጀምራል መወትወት - ያልጠየቁትን ማተት

"ሁልሽም ትሞቺያለሽ ከኔ ቀድመሽ
በወባ … በትንኝ … በቢምቢ ተነድፈሽ

ይለናል የኛ ሠፈር - ጣጤ
ብርቱካን ሆኖበት ኮምጣጤ

ጣጥ ሲል የኛ ሠፈር ሰው በብርቱ
አያውቀውም የሚተፋውን ባንደበቱ

ማርም አይጥማት ለዚያችቱ
ደክማ … ዳገት ወጥታ ወራጅቱ
እንደ ሠፈራችን ሰው - እንደ ጣጤ
ዲሞክራሲ … እንቆቆ …ብርቱካን ኮምጣጤ

ሲፈተፍት በሰው ጉዳይ የኛው - ጣጤ
ብርቱካን ሆኖበት ኮምጣጤ

ሹመት በወሬ
አውሊያ - ትምቢት ነጋሪ
ዘር ቆጥሮ ጠጁን ደንቃሪ
ዲሞክረሲ? ቅራሪ …
ምንትስ ሁሉ … አደናጋሪ

ይለናል የኛ ሰፈር ሰው - ጣጤ
ብርቱካን ሆኖበት ኮምጣጤ